# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

## የ1998 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት
## ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

አዲስ አበባ
ጥቅምት 1998

# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

## የ1998 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት
## ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

አዲስ አበባ

ጥቅምት 1998

# ማውጫ

አርዕስት ገጽ


1. መግቢያ ..................1
2. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ ..................3
   2.1 የተፈጥሮ ሃብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት ..................3
   2.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት ..................5
   2.3 የኢንዱስትሪ፣ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት ..................6
3. የሥነ - ሕዝብ ስታቲስቲክስ ..................8
   3.1 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት ..................8
   3.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ..................10
4. 1997 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም ..................15
5. ሳምፕሊኒንግ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ ..................17
6. የመረጃ ማቀነባበርን በተመለከተ ..................18
7. የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ..................19
8. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት ዝግጅትን በተመለከተ ..................20
9. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ..................21
10. የኦዲት አገልግሎት ..................22
11. የሕግ አገልግሎት ..................22
12. የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት ..................23
13. የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት ..................23
   13.1 የሰው ኃይል ሁኔታ ..................24
   13.2 የበጀት አጠቃቀም ..................25
   13.3 አገልግሎት ነክ የሆኑ ጉዳዮች ..................28
14. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ..................30

# 1998 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት
# የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

መንግሥት ለሚያወጣቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች፣ እንዲሁም በነዚህ ፖሊሲዎች ላይ በመመርኮዝ የሚታቀዱትን የልማት ዕቅዶች አፈፃፀም ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስታቲስቲካዊ መረጃ በየዘርፉ መገኘት ለሃገር ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝነት አለው።

•

በዚህ ረገድ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የአገሪቱን መሠረታዊ የስታቲስቲክስ መረጃዎች ፍላጎት ለማሟላት በየጊዜው ጥረት እያደረገ ይገኛል።

በመሆኑም መ/ቤቱ በየጊዜው አዳዲስ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶችን በመቀየስ፣ በመንደፍና በመቅረጽ እጅግ በርካታ የሆኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማቀነባበር፣ በመተንተንና በሪፖርት በማውጣት ለተጠቃሚዎች እያሠራጨ ይገኛል። እነዚህም መረጃዎች እንደተገልጋዩ ፍላጐት ለዕቅድም ሆነ ለምርምር እንደዚሁም ለሌሎች ሥራዎች መነሻ በመሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛሉ።

በ1998 በጀት ዓመት መ/ቤቱ የአምስት ዓመቱን የስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት በማድረግ ለማከናወን ያቀዳቸው የስታቲስቲክስ ጥናቶች ከላይ የተገለፀውን አጠቃላይ መርህ ለማሣካት ያለሙ ሲሆን፣ ጥናቶቹ የመ/ቤቱን የማስፈጸም አቅምና የተመደበለትን በጀት ግምት ውስጥ በማስገባት የታቀዱ ናቸው።

በዚህም መሰረት የመረጃ መሰባሰቡ ተግባር በ1997 ዓ.ም ተጀምሮ የመረጃ ማቀነባበሩ ተግባር ወደ 1998 የተሸጋገሩ የበልግ ወቅት የግብርና ናሙና ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ የግልና የመንግስት እርሻዎች ጥናት፣ የአትክልት፣ ሥራ ሥርና የቋሚ ሰብሎች የ1996 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንድስትሪ ጥናት፣በውጭ ዕርዳታ የሚከናወን የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ ቀሪ ሥራዎችን እንዲሁም በበጀት ዓመቱ የሚጠኑ በርካታ አዳዲስ ጥናቶችን በማከናወን ላይ ይገኛል። እነዚህም ጥናቶች፣

ሀ. የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት
- የሰብል ምርት ጥናት በመኸር ወቅት

- የሰፋፊ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ጥናት
- የሰብል ምርት ጥናት በበልግ ወቅት
- የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ኃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናት /በገጠር/

ለ የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ

- የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት /በከተማ/
- ወቅታዊ የማምረቻ የንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት /በከተማ/
- የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የምርት መጠንና የአምራቾች ዋጋ ጥናት በየሩብ ዓመት /በከተማ/
- የኮንስትራክሽን ጥናት
- የማዕድንና ቁፋሮ ጥናት
- የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት
- የውጪ ንግድ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር
- የትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር፣

ሐ የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

- የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት /በገጠር/
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት /በከተማ/
- የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶች ዝግጅት /በዋናው መ/ቤት/
- የዓለም አቀፍ የንፅፅር ፕሮግራም

መ የማኅበራዊ ስታቲስቲክስ

- ወቅታዊ የሥራ ስምሪት ጥናት

ሠ የቆጠራ ካርታ ሥራ ማካሄድ ናቸው።

## 2. የኢኮኖሚ ስታቲስቲክስ

### 2.1 የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ

#### 2.1.1 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናትን በተመለከተ

- የ1998 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት መረጃ የተሰበሰበባቸው መጠይቆች ዋናው መ/ቤት የደረሱ ሲሆን ለኤዲቲንግና ቬሪፊኬሽን ሠራተኞች ስልጠና በመስጠት የእርማትና የቬሪፊኬሽን ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

- ለ1998 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ለቬሪፊኬሽን ሥራ የሚያገለግል መመሪያና ኮድ ቡክ አሻሽሎ በማዘጋጀት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

#### 2.1.2 የእርሻ መሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃ በተመለከተ

- የ1997 ዓ.ም የበልግ ወቅት ጥናት መረጃን በሚመለከት ኤዲት፣ ኮድና ቬሪፋይ ለሚያደርጉ ሠራተኞች ሥልጠናውን በመስጠት የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና የቬሪፊኬሽን ሥራ ተካሂዷል፡፡

- የ1997 ዓ.ም የበልግ ወቅት የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን የመረጃ ቅንብሩ ተግባር፣ የትንተናና የሪፖርት ዝግጅቱ ሥራ ተጠናቆ ለህትመት ዝግጁ ሆኗል፡፡

#### 2.1.3 የመሬት አጠቃቀም

የ1997 ዓ.ም የመኸር ወቅት የመሬት አጠቃቀም (Land use) ጥናት ውጤት ስታቲስቲካል ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡

#### 2.1.4 የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታን በተመለከተ

- የ1997 ዓ.ም የመኸር ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት ውጤት የሆነው የስታቲስቲካል ሪፖርት ዝግጅትና ሕትመት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

- በ1997 ዓ.ም ከመስክ የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀበት የበልግ ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት በኮምፒውተር የማቀነባበሩና የትንተናው ሥራ ተጠናቆ ለህትመት ዝግጁ ሆኗል፡፡

### 2.1.5 የቤት እንስሳት የዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎችን በተመለከተ

የ1998 ዓ.ም የቤት እንስሳት ዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናትን በሚመለከት ለመረጃ መሰብሰብ ተግባር የሚያገለግል የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ለመረጃ ቅንብሩ ውጤት ማስፈሪያ የሚያገለግል የTabulation Plan ዝግጅት በመካሄድ ላይ ይገኛል።

### 2.1.6 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- ለ1998 ዓ.ም የቅድመ ማስጠንቀቂያ ለመኸር ለበልግ ወቅትና ለቋሚ ሰብል ምርት ትንበያና ለግብርና ናሙና ጥናት ከመስክ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችና አዳዲስ ቅጾችን ያካተቱ መጠይቆችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ውለዋል።

- ለ1998 ዓ.ም የቅድመ ማስጠንቀቂያ የሰብል ምርት ትንበያ ለዋናው መኸር ግብርና ናሙና ጥናት፣ ለቤት እንስሳት ጥናት ለበልግ ወቅት ግብርና ጥናት፣ ለሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎችን በተመለከተ በነሐሴ አጋማሽ ጀምሮ ለ20 ቀናት በ25ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ለሚገኙ መረጃ ሰብሳቢዎችና ለመስክ ሥራ ተቆጣጣሪዎች ሥልጠና ተሰጥቷል።

- በ1998 ዓ.ም ለሚካሄደው የምግብ ዋስትና ጥናት ማዘጋጃ የሚያገለግሉ Tabulation Plan ዝግጅት ሥራ በመሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በግብርና ቆጠራ መረጃ ላይ መሠረት ያደረገ ለኢትዮጵያ ግብርና አትላስ ዝግጅት የሚያገለግል የትርጉም ሥራም ተከናውኗል።

- መ/ቤቱ በየዓመቱ ለሚያዘጋጀው ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት መምሪያውን የሚመለከት መረጃዎች ከሌሎች መ/ቤቶች የማሰባሰብና በመምሪያው የሚገኙትንም የማጠናቀር ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛል።

- ከተለያዩ መ/ቤቶችና ድርጅቶች ለሚቀርቡ የመረጃ ጥያቄዎች ተገቢው ምላሽ ተሰጥቷል።

## 2.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

### 2.2.1 የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክስን በተመለከተ

#### ሀ. በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት

- የሐምሌ ወር 1997 ዓ.ም የአምራቾች ዋጋ ጥናት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።
- የነሐሴ ወር 1997 ዓ.ም መረጃ ተቀነባብሮ ለህትመት ተዘጋጅቷል።

#### ለ. ወርሐዊ የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት

የሐምሌ 1997 ዓ.ም ያለው ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች የተሠራጨ ሲሆን፣ የ1997 የነሐሴ ወር መረጃም ተቀነባብሮ ለህትመት ተዘጋጅቷል።

#### ሐ. ወርሃዊ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ

- የሃገር አቀፍና የክልሎች
  - የሀገር አቀፍና የክልሎች የሸማች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ እስከ ነሐሴ 1997 ዓ.ም ያለው መረጃ በየወሩ ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል።
  - የመስከረም ወር 1998 ዓ.ም ጠቋሚ አሃዝ ተቀነባብሮ ለህትመት ዝግጁ ሆኗል።

- የአዲስ አበባ ከተማ
  - የአዲስ አበባ ከተማ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ እስከ መስከረም 1998 ዓ.ም ያለው መረጃ በየወሩ እየተቀነባበረና እየታተመ ለተጠቃሚዎች በወቅቱ ተሰራጭቷል።

### 2.2.2 የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናትን በተመለከተ

በሁለት ዙር የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ተጠናቀቀለት የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት መረጃ የማጥራት ሥራ ተከናውኖ የመጀመሪያው ውጤት ለቅድመ

ዝግጅት ሥራዎች እንዲውል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የተሰጠ ሲሆን፤ የመጨረሻው መረጃውን የማጥራት ተግባር እየተከናወነ ይገኛል፡፡

### 2.2.3 የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናትን በተመለከተ

በ1996 በጀት ዓመት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት የመረጃ ማቀነባበርና አጠቃላይና የሪፖርት ዝግጅቱ ተጠናቆና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

### 2.2.4 ዓለም አቀፍ የንፅፅር ፕሮግራም - በአፍሪካ

ይህንን ጥናት በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ለማካሄድ በሁለት ምዕራፍ የሚከናወን መርሃ - ግብር ተዘጋጅቷል፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያው ምዕራፍ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባሉ 12 የገበያ ቦታዎች ላይ ለማካሄድ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡ በመጀመሪያው በጀት ዓመት የጥናቱን የመረጃ መሰብሰቢያ ማንዋልና መጠይቅ የመተርጐም ተግባር ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ሲሆን፤ በመረጃ መሰብሰብ ተግባር ላይ ለሚሣተፉ መረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች ስልጠና ተካሄዶ ወደ ሥራ ተሰማርተዋል፡፡

### 2.2.5 ልዩ ልዩ ሥራዎች

መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀው ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት የሚያገለግሉ ዘርፉን የሚመለከቱ መረጃዎች ከልዩ ልዩ መ/ቤቶች የማሰባሰቡ ተግባር ተጀምሯል፡፡

## 2.3. የኢንድስትሪ፣ንግድ ትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስ

### 2.3.1 የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ ጥናቶችን በተመለከተ

#### ሀ. የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት

- በ1997 የዕቅድ ዘመን የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የ1996 በጀት ዓመትን የሚመለከተው የዘርፉ ጥናት የመረጃ ቅንብርና ትንተና ሥራው በአብዛኛው ተጠናቆ ለህትመት በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

- የ1997 የአራተኛ ሩብ ዓመት የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ወቅታዊ ጥናት ከመረጃ መሰብሰብ እስከ ሪፖርት ዝግጅት ድረስ ያለው ሥራ ተከናውኖ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

- የ1997 የአራተኛ ሩብ ዓመት የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የዋጋ ጥናት የመረጃ መሰብሰብና ኤዲቲንግ ሥራው የተካሄደ ሲሆን የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የዋጋ ኢንዴክስ (PPI) እየተሰራ ነው፡፡

ለ. <u>የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት</u>

በየ1998 ሊካሄድ የታሰበው የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የመጠይቅና የማንዋሎች ዝግጅት ሥራ ተከናውኗል፡፡

ሐ. <u>የኢኮኖሚ ድርጅቶች ቆጠራ</u>

በ1995 ዓ.ም ጥናቱ የተካሄደለት የኢኮኖሚ ድርጅቶች ቆጠራ መረጃን ጥራት ለማሻሻልና ዳታ ቤዝ ለመፍጠር ከዓለም ባንክ ከተላኩ አማካሪ ጋር በመሆን በርካታ ሥራዎች ተከናውኗል፡፡

መ. <u>የንግድ፣ ትራንስፖርት፣ መገናኛና ፋይናንስ ስታቲስቲክስ</u>

- ለትራንስፖርትና በመገናኛ መጽሔት የሚሆኑ መረጃዎች ከየመሥሪያ ቤቶች የመሰብሰብ ሥራ ተከናውኗል፡፡
- ለዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆኑ የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃዎች የመሰብሰብ ተግባር እየተከናወነ ይገኛል፡፡
- ለአከፋፋይ ንግድ ጥናት የሚሆን የመጠይቅ ዝግጅት ሥራ እንዲሁም የሙከራ ጥናት በሦስት ከተሞች ማለትም በአዲስ አበባ፣ ፍቼና ደብረብርሃን ተከናውኗል፡፡
- የውጭ ንግድ መረጃ ለጠየቁ መረጃ ተጠቃሚዎች አስፈላጊው መረጃ ተሰጥቷል፡፡

ሠ. <u>ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች</u>

በዚህ ዓመት ለሚካሄዱ ጥናቶች በፍሬምነት የሚያገለግሉ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የግንባታ ሥራ ተቋራጮች፣ በድንጋይ አሸዋና ሌሎች ማዕድናትን በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ዝርዝር የመወጣት ሥራ ተከናውኗል፡፡

## 3. የሥነ- ሕዝብ ስታቲስቲክስን በተመለከተ

### 3.1 የማህበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ

#### 3.1.1 የሰው ሃይል ስታቲስቲክስ

- በ1997 ዓ.ም የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የሰው ሃይል ጥናትን በሚመለከት ለኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያ ተዘጋጅቶ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ የተሰበሰበው መረጃ በአብዛኛው የኤዲቲንግ ሥራ ሲከናወን፣ 64% የሚሆነው ከተሞችን የሚመለከተው መረጃ ደግሞ ቬሪፋይ ተደርጓል፡፡

- ከሰው ኃይል ጥናት መጠይቅ ውስጥ 38% የሚሆነው መረጃ ወደኮምፒውተር የገባ ሲሆን፣ የኤዲቲንግ ስፔስፊኬሽንና የምስል ሠንጠረዥ ዝግጅት ተጠናቆ የክሊኒንግ ሥራም ተጀምሯል፡፡

#### 3.1.2 የትምህርት፣ ባህልና ስፖርት ስታቲስቲክስን በተመለከተ3

- ለ1997 ዓ.ም ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚያስፈልጉ የትምህርት፣ የባህልና ስፖርት፣ የጤና፣ የህግና ደንብ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ መጠይቆች ተዘጋጅተዋል፡፡

- የ1997 ዓ.ም ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት መረጃዎች የሚሰበሰቡበት ቅጾች፣ እንዲሁም በ1996 ዓ.ም ከክልል ተሞልተው የመጡ የትምህርት መጠይቆች ተፈትሸው የታዩ ጉድለቶች እንዲስተካከሉ ለማድረግ አንድ ጥራዝ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ተልኳል፡፡

- ለ1997 ዓ.ም ዓመታዊ መጽሔት ዝግጅት የሚረዱ የ1996 ዓ.ም የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጾች ተዘጋጅተው በአዲስ አበባ ለሚገኙ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል ቢሮዎች ተሰጥቷል፡፡

- ለዓመታዊ መጽሔት ዝግጅት መረጃዎች ከክልልና ከፌደራል መ/ቤቶች ተሞልተው ሲመጡ ወደ ኮምፒውተር የሚገቡበትና የሚጠናቀሩበት፣ እንዲሁም መጽሔት ታትሞ ሲወጣ ተጠቃሚዎችን የሚያረካ እንዲሆን የሚያስችል ሠንጠረዥ ተዘጋጅቷል፡፡

3.1.3 የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስ በተመለከተ

- የ1997 ዓ.ም ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚያስፈልጉ የህግና ደንብ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚያስችሉ መጠይቆች ተዘጋጅተዋል፡፡

- በ1996 ከክልል ተሞልተው የመጡ የትምህርት መጠይቆች ላይ የተዩ ጉድለቶችን የያዘ ጥራዝ ተዘጋጅቶ ወደፊት ጉድለቶቹ እንዳይደገሙ ለማድረግ ለሚመለከታቸው የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ተልኳል፡፡

- ለ1997 ዓመታዊ መጽሔት ዝግጅት የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጾች ለስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶችና በአዲስ አበባ ውስጥ ለሚገኙ ለሚመለከታቸው ለፌደራልና ለክልል ቢሮዎች ተሰጥቷል፡፡

- ለዓመታዊ መጽሔት ዝግጅት መረጃዎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ተሞልተው ሲመጡ ወደ ኮምፒውተር የሚገቡበትና የሚጠናቀቁበት የሠንጠረዦች ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

- ከሁለተኛ ምንጭ የሚገኙ መረጃዎችን ይዘት ለማሻሻል ከመረጃ ሰጭ መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሊገኙ የሚችሉ መረጃዎችን ለማጥናት የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

3.1.4 <u>የጤናና አመጋገብ</u>

- ቀደም ሲል የተዘጋጀውን የኤች. አይ. ቪ. /ኤድስ የባህርይ ቅኝነት ጥናት የኤዲቲንግና የኮዲንግ ማንዋል ግምገማ ተካሄዷል፡፡

- በባህርይ ቅኝት ጥናቱ በተካተቱ በአዲስ አበባ በሚገኙ 25 ት/ቤቶች ውስጥ ከተሰበሰበው መረጃ የወንድ ተማሪዎች 786፣ የሴት ተማሪዎች 888 እንዲሁም የመምህራን 97 መጠይቆች የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ተጠናቋል፡፡

- የባህርይ ቅኝት ጥናትን በተመለከተ መረጃዎች ሊጠናቀሩበት የሚችሉ የሠንጠረዥ ዝግጅትና ከሚመለከታቸው ተቋማት (ከወረዳዎች ወይም ከጤና ተቋማት) ተጨማሪ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚያስፈልጉ የመሠረታዊ መረጃዎችን አይነት የመለየት ሥራ ተጠናቋል፡፡

- በዓለም ጤና ድርጅት በ Health Net work matrix አማካይነት ለመምሪያው ምን ዓይነት ርዳታ እንደሚያስፈልገው የሥራ ዝርዝሮችና የገንዘብ መጠንን በተመለከተ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ተልኳል፡፡

### 3.1.5 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- ለተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የአገልግሎት እገዛ ተደርጓል፡፡
- ለተለያዩ መረጃ ጠያቂዎች ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

## 3.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በተመለከተ

### 3.2.1 የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ

በአገራችን ለ3ኛ ጊዜ በ1999 ዓም ሊካሄድ ለታሰበው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ተግባራት ሲካሄዱ ቆይተዋል፡፡ ከነዚህ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መካከል ለቆጠራው የመስክ ሥራ ክንውንና ለሌሎች የዝግጅት ሥራዎች አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እንዲያስችል በቆጠራ ቦታ የካርታ ሥራ አገሪቷን በቆጠራና በመቆጣጠሪያ ቦታዎች የመሸንሸን ተግባር ከነሐሴ ወር 1995 ጀምሮ በተለያዩ ክልሎች እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡

ይህ የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ከ1995 ዓም ጀምሮ እስከ መጋቢት 1997 ድረስ በ45 ቡድኖች ሲሠራ ቆይቶ ከ1997 መጋቢት ወር አጋማሽ አንስቶ ሌሎች 49 አዲስ ቡድኖችን በመጨመር በድምሩ በ94 ቡድኖች በያዝነው የበጀት ዓመት በተለያዩ ክልሎች የካርታ ሥራው በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ከሐምሌ ወር 1997 ጀምሮ የቆጠራ ካርታ ቦታ ሥራ በጀት ወደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መላክ በመጀመሩ አብዛኛው አስተዳደራዊ ሥራዎች በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመከናወን ላይ ቢሆንም የሥነ ሕዝብ ማስተባበሪያ የቴክኒክ ሥራዎችንና የተወሰኑ የአስተዳደር ሥራዎችን አከናዉኗል፡፡ እነዚህም

- ለቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ የሚያስፈልጉ የመነሻ ካርታዎች፣ የተለያዩ ቅጾችና የጽሕፈት መሣሪያዎችን በማደራጀት ወደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲላኩ ተደርጓል፡፡

- ከየቦታዉ ለሚነሱ የቴክኒክ ጥያቄዎች ተገቢዉ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡
- የተጠናቀቁ የቆጠራ ቦታ ካርታዎችና ዶኩሜንቶች ርክክብ ተፈፅሟል፡፡
- ለቆጠራ ቦታ ካርታ የመስክ ሥራ ላይ የተመደቡ ተሽከርከሪዎች ከሰኔ 30 ቀን 1997 በኋላ የአብዛኞቹ ተሽከርካሪዎች የሰርቪስ ጊዜያቸው በመድረሱ ጋራዥ ገብተው በወቅቱ ተጠግነው እንዲወጡና ወደ መስክ እንዲሠማሩ አስፈላጊው ክትትል ተደርጓል፡፡
- የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራዉ በተሰጠዉ መመሪያ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን ለመቆጣጠርና ለመገምገም እንዲሁም በሠራተኞች መካከል ጥሩ የሥራ ዲስፕሊን መኖሩን ለማረጋገጥ በየመምሪያው ያሉ የቴክኒካል ኮሚቴ አባላት ከነሐሴ 14 ቀን 1997 ጀምሮ እስከ ነሐሴ 28 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ የመስክ ጉብኝት እንዲወጡ በማድረግ ከሞላ ጎደል የሁሉም ቡድኖች ሥራ እንዲታይ ተደርጓል፡፡
- ከመስክ ተጠናቀው የተላኩ የቤተሰብ ምዝገባና የኮኦርዲኔቶች ዝርዝር በተዘጋጀው የዳታ ኢንትሪ ፕሮግራም መሠረት በኮምፒውተር የመቅረጽ ተግባር ተከናውኗል፡፡
- በጂ.አይ.ኤስ በመታገዝ የቆጠራውን ውጤት ለተጠቃሚ ለማቅረብ የ8 ወረዳዎች ካርታ በቀጣይነት ዲጂታይዝድ የማድረግ ሥራዎችና የገጠርና የከተማ የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጾች /ገ-2 እና ከ-2/ና የድንበርና የውስጥ ገጽታዎች መመዝገቢያ ቅጽ /ገ-6/ መረጃዎችን ኤዲትና ኮድ በማድረግ የ10 ወረዳዎች በኮምፒውተር የመቅረጽ ሥራዎችና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎች ተከናውኗል፡፡

### 3.2.2 <u>ሌሎች የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በተመለከተ</u>

ለሦስተኛ ጊዜ በሚካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ለሚሰበሰቡ የልደት፣ የሞት፣ የፍልሰትና የአሠፋፈር መረጃዎችን ከዚህ ቀደም ከነበረው በተሻለ ሁኔታ ለመሰብሰብ እንዲቻል በሁለተኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ላይ የዋሉትን መጠይቆች መመርመር ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ባለፈው የበጀት ዓመት በመምሪያው ሥር ያሉት የልደትና ሞት ስታቲስቲክስ ፣ የፍልሰትና አሠፋፈር ስታቲስቲክስ፣ የትንበያ ስታቲስቲክስ ቡድኖች በዕቅዱ መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ የመጠይቆች ግምገማ አካሂደው ግርድፍ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡

### 3.2.3 ሁለተኛው ዙር የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናትን /DHS/ በተመለከተ

የዓለም አቀፍ የናሙና ጥናት ፕሮግራም አካል የሆነውን የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት ባለፈው የበጀት ዓመት በአገሪቱ ለሁለተኛ ጊዜ ለማካሔድ በዕቅድ ተይዞ የመስክ ሥራው ከመጋቢት ወር 1997 አጋማሽ ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1997 ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በሥነ ሕዝብ ማስተባበሪያ ሥር የሚገኙ መምሪያዎች በ1998 በጀት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት አከናውኗል፡፡

- በተለያዩ መምሪያዎች ሥር የሚገኙ ባለሙያዎች በተለያዩ ክልሎች መስክ በመውጣት የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት የሥራ ሂደት የቴክኒክና የአስተዳደር ሥራዎች ማለትም የተሞሉ መጠይቆችን ኤዲት በማድረግና የመረጃ አሞላል ሂደቶችን በመመርመር፣ የተሽከርካሪዎች አቅርቦትና ሥርጭት፣ የደመወዝና የውሎ አበል አከፋፈል፣ በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ያሉ መረጃ ሰብሳቢዎች የሥራ ድርሻቸውን አውቀው በጥሩ የስራ ዲስፕሊን የተጣለባቸውን ኃላፊነት እየተወጡ መሆናቸው ተገምቷል፡፡

- በተለያዩ መምሪያዎች ሥር ከሚገኙ ባለሙያዎች መካከል 11 አስተባባሪዎችን በመመደብ ለመስክ ሠራተኞች ደመወዝ፣ አበልና የሥራ ማስኬጃ በወቅቱ እንዲደርሳቸው በማድረግ እንዲሁም የቴክኒክና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ በቅርብ በመሆን ቁጥጥር እንዲያደርጉ ተገቢውን ክትትል ተደርጓል፡፡

- ከመስክ ለሚነሱ የቴክኒክ ጥያቄዎችና አስተዳደራዊ ጉዳዮች /የተሽከርካሪ ብልሽት፣ የትብብር ማነስ፣ በሠራተኞች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች.... ወዘተ/ አፋጣኝ መፍትሔ መፈለግና የመስክ ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላም የተሞሉ መረጃዎችና የመስክ ቁሳቁሶች ርክክብና ሌሎች ተያያዥ አስተዳደራዊ ሥራዎች ክንውንን ለመከታተል ተችሏል፡፡

- ከመስክ የተሞሉ ቅጾችና መጠይቆችን ሁለት ዙር ኤዲት በማድረግና ኮድ ማድረግ /በ4 ዳታ ኤዲተሮች እና በ22 ዳታ ኢንኮደሮች/፣ መረጃውን ወደ ኮምፒውተር ማስገባት፣የመረጃ እርማት /Data Cleaning/ እና የመረጃ የማቀነባበር (Data Processing) ሥራዎች በተያዘላቸው ጊዜ መፈጸማቸውን ክትትል ተደርጓል፡፡

- ከዐብይ ኮሚቴ (Steering Committee)ና የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ጋር በየጊዜው ግንኙነት በማድረግ በሥራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን የመፍታት ሥራ ስብሰባዎች ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ እንዲሁም ለጥናቱ ቴክኒካዊ ዕገዛ ከሚያደርገው (ORC - MACRO) በየወቅቱ /በስልክ፣ በኢሜል፣ በአካል… ወዘተ/ በመገናኘት የጥናቱ ቀሪ ሥራዎች በተያዘላቸው ፕሮግራም መሠረት ስለሚጠናቀቁበት መንገድ አስፈላጊውን መረጃ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

- በተለያዩ ክልሎች በሚካሄደው የመስክ ሥራና በቢሮ ኤዲቲንግ ላይ የሚያጋጥሙ ቴክኒካዊ ችግሮችን ከአስተባባሪዎችና ከቡድን ተቆጣጣሪዎች ጋር በመነጋገር የመፍትሔ ሃሳብ በማቅረብና በተለይም በአዲስ አበባ መስተዳድር የተሠማሩትን ሦስት ቡድኖች በቅርብ ቁጥጥር በማድረግ የሚሰበሰበው መረጃ ጥራት እንዲስተካከል አስፈላጊው ጥረት ተደርጓል፡፡

- ከመስክ የሚሰበሰበውን የደም ናሙና ከአስተባባሪዎች በጥንቃቄ በመረከብ ምርመራው ወደሚካሄድበት የኢትዮጵያ የሥነምግብ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት በወቅቱ ማስረከብ ተችሏል፡፡

- የጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት (Preliminary Report) ዝግጅትን የመከታተል ሥራዎች ተከናውኗል፡፡

### 3.2.4 <u>የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስን በተመለከተ</u>

ባለፉት ዓመታት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶችን በመላ አገሪቱ ለማቋቋም፣ ለማደራጀትና ለማካሄድ የሚያስችሉ የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ተግባራት ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜያት ጀምሮ ደግሞ ወደፊት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚቋቋሙት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶች በሕግ፣ በቴክኒክ፣ በአስተዳደር፣ በበጀትና በሰው ሃይል ድልድል በኩል ሊያገጥሙአቸው የሚችሉ ችግሮችን ለማጥናት የሚያስችል በተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) የገንዘብና በጽ/ቤቱ የቴክኒክ ድጋፍ በደቡብ ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ በአማራና በትግራይ ክልሎች ሞዴል የምዝገባና ስታቲስቲክስ ፕሮግራም ከመጋቢት 1 ቀን 1997 ጀምሮ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ እነዚህም

- የዚህን ፕሮግራም አጠቃላይ ሂደት መከታተልና መገምገም እንዲቻል የሞዴል ፕሮግራሙ በሶስት ክልሎች ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ በቴክኒክ፣ በገንዘብ፣ በአስተዳደርና በአደረጃጀት፣ በሰው ሃይልና በአፈጻጸም ረገድ ያጋጠሙትን ችግሮች ለመገምገም ከበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ የቫይታል ስታቲስቲክስ መምሪያው አባላት በተለያዩ ቡድኖች በመከፋፈል ከሰኔ 25/1997 እስከ ሐምሌ 1/1997 በደቡብ ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በ14 የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች፣ በአማራ ክልል ከሐምሌ 20 ቀን 1997 - ሐምሌ 29 ቀን 1997 በክልሉ ለሞዴል የምዝገባ ፕሮግራሙ ከተመረጡት 32 የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች ውስጥ በ27ቱ የመስክ ጉብኝት ተደርጓል።

- ከዚህም ሌላ ሁለት አባላት ያሉት ቡድን በትግራይ ክልል በተለያዩ ወረዳዎች በመካሄድ ላይ ያለው ሞዴል የምዝገባና ስታቲስቲክስ ፕሮግራም በቴክኒክ፣ በአስተዳደርና በአፈጻጸም ረገድ ባጋጠሙት ችግሮችና የተገኙ ልምዶች በሚገመግም መስከረም 7 ቀን 1998 በመቀሌ ከተማ በተካሄደ ስብሰባ ላይ ተሳትፏል። በዚህም ወቅት በስብሰባውም ላይ ቡድኑ በምዝገባ ቅጾቹ ላይ ስለተደረጉ ለውጦችና በሞዴል ፕሮግራሙ ላይ ስለተሰራው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኮምፒውተር ፕሮግራም ማብራሪያ ሰጥቷል።

- በሶስቱም ክልሎች በተካሄዱ ጉብኝቶች ቡድኖች በመስክ በመገኘት ሥራውን ከሚያከናውኑ መዝጋቢዎች፣ ከአስተባባሪዎችና ከየወረዳው ሥራ አስፈጻሚዎችና ክክልል የሥራ ኃላፊዎች ጋር በቴክኒካዊ፣ በአስተዳደራዊና የበጀት ጉዳዮች ላይ በመወያየት የክልሉን ሞዴል የምዝገባና ስታቲስቲክስ ፕሮግራም በመገምገምና የፕሮግራሙን ደካማና ጠንካራ ጎኖች የመለየት ተግባራትን የሚዳስስ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት አቅርቧል።

- ከዚህም ሌላ አንድ የመምሪያው ባልደረባ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስቴር የሚመራ የመልእክተኞች ቡድን አባል ሆኖ ከመስከረም 16 እስከ መስከረም 20 ቀን 1997 በኬንያ የወደብ ከተማ በሞምባሳ በተካሄደው የምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ አገሮች "የሕጻናትን መብቶች ለመጠበቅ የልደት ምዝገባ አገልግሎቶችን ማሻሻል "Improving Services to Protect the Rights of Children: Universal Birth Registration conference" በሚል ርእስ ላይ በተወያየ ስብሰባ ላይ ተገኝቷል። የልዑካኑ ቡድን በስብሰባው ላይ የሚቀርበውን አገራዊ ሪፖርት ጽ/ቤቱ አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ በጠየቀው መሠረት የአገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ያለበትን ደረጃ የሚገልጽ 30 ገጾች ያለው አንድ ጥናታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ አቅርቧል።

### 3.2.5 ሌሎች ተግባራትን በተመለከተ

- የኔት ወርክ አድሚንስትሬሽና በኮምፒውተር የተሠሩ ሥራዎችን መጠባበቂያ / Backup/ የመያዝ እና የመሳሰሉት ሥራዎች ተሰርተዋል።

- ከመረጃ ጠያቂዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በማስተናገድ አስፈላጊ የሙያ ድጋፍ ተደርጓል።

## 4. የ1998 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

በ1998 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው አዳዲስ ጥናቶችንና ከ1997 የተሸጋገሩ ቀሪ ሥራዎችን ለማከናወን በዕቅድ መያዙንና በበጀት ዓመቱ ያከናወናቸውን ሥራዎች በዝርዝር ቀርበዋል። የእነዚህን ጥናቶች የፊዚካል አፈፃፀም በተመለከተ ደግሞ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1   በ1998 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | የጥናቱ ዓይነት | ጥናቱ የሚገኝበት ደረጃ | እስከ 1997 በጀት ዓመት መጨረሻ የተከናወነ | የመጀመሪያ ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
| 1 | የ1998 የግብርና ናሙና ጥናት | | | | | |
| 1.1 | የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት | አዲስ | 6.49 | 38.51 | 38.51 | 100 |
| 1.2 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት የመኸር ወቅት | | | | | |
| | • የታረሰ መሬት ናሙና ጥናት | አዲስ | 6.49 | 16.95 | 16.95 | 100 |
| | • የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ | አዲስ | 6.49 | 23.51 | 23.51 | 100 |
| | • የመሬት አጠቃቀም | አዲስ | 6.49 | 23.51 | 23.51 | 100 |
| 1.3 | የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች ጥናት | አዲስ | 6.43 | 8.51 | 8.51 | 100 |
| 1.4 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት የበልግ ወቅት | አዲስ | 6.43 | 8.51 | 8.51 | 100 |
| 1.5 | የሰፋፊና መካከለኛ የድርጅት እርሻዎች ጥናት | አዲስ | 6.43 | 8.51 | 8.51 | 100 |
| 1.6 | የ1997 የግብርና ምርት ናሙና ጥናት በበልግ ወቅት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 23.63 | 67 |
| 2 | የግብርና ዉጤቶች የአምሮቾች ዋጋ ጥናት | አዲስ | 3.00 | 30.49 | 30.49 | 100 |
| 3 | የችርቻሮ ዋጋ ጥናት | አዲስ | 3.00 | 33.26 | 33.26 | 100 |
| 4 | የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት | ነባር | 90.00 | 10.00 | 10.00 | 100 |
| 5 | የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት | ነባር | 65.00 | 12.52 | 8.52 | 68 |
| 6 | ዓለም አቀፍ የንፅፅር ፕሮግራም በአፍሪካ | ነባር | 6.36 | 17.88 | 17.88 | 100 |
| 7 | ወቅታዊ የማምረቻ፣የንግድና የአገ.ሰጪ ድርጅት | አዲስ | - | 3.46 | 3.46 | 100 |
| 8 | የማምረቻ ኢንድስትሪ የምርት ዋጋ ኢንዴክስ | አዲስ | 15.00 | 21.52 | 21.25 | 100 |
| 9 | የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት | አዲስ | - | 6.68 | 6.68 | 100 |
| 10 | የ1996 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ.ጥናት | ነባር | 65.00 | 32.78 | 32.78 | 100 |
| 11 | የ1997 የሰው ኃይል ጥናት | ነባር | 65.00 | 9.61 | 9.61 | 100 |
| 12 | ለኤች.አይ.ቪ በምክንያት የሚጠቀሱ ባህርያት ጥናት | ነባር | 65.00 | 6.25 | 6.25 | 100 |

## 5. ሣምፕሊንግ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ

- የ1997 የሰው ሃይል ጥናትን በሚመለከት ለማባገር የሚያገለግሉ በየቆጠራው ቦታ የተመዘገቡ ቤተሰቦች ብዛት ከየቆጠራ ቦታው የመልቀም ሥራ ተካሄዶ የ Weight እና Rate ፎርማት ተዘጋጅቶ በየቆጠራ ቦታው የተለቀሙትን ቤተሰቦች ብዛት ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ሥራ ተጠናቋል።

- የ1997 ዓ.ም የበልግ ወቅት ግብርና ናሙና ጥናት ለመሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት እንዲሁም ለእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት Weight እና Rate ዝግጅት፣ እንዲሁም የናሙና ጥናቱ አስተማማኝነት (CV) ግምገማና የሜቶዶሎጂ ሪፖርት ዝግጅት ሥራ ተጠናቋል።

- የ1998 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናትን በአዲስና በተሻሻለ ሁኔታ ለማካሄድ በታቀደው መሠረት አዲስ የናሙና ቦታዎች ብዛት ድልድል በዞን ደረጃ ተከናውኗል። እንዲሁም በአዲሱ አሠራር መሠረት የቤተሰቦችን አመዘጋገብና የናሙና አመራረጥን የሚያመለክትና የሚያብራራ ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎቹ መመሪያ ተዘጋጅቷል።

- ለ1998 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናት የናሙና ቆጠራ ቦታዎችንና የሠፈራ መንደሮችን ዝርዝር የያዘ ኮድ ቡክ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ተሠራጭቷል።

- ለ1998 ግብርና ናሙና ጥናትና ለ1997 ዓ.ም የሰው ሃይል ጥናት የአካባቢ መለያን በሚመለከት ለኤዲተሮችና ኮደሮች ስልጠና ተሰጥቷል።

- በኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ቆጠራ ወቅት ከመረጃ ማቀነባበሪያ የተገኙ የቆጠራ ቦታዎችን ዝርዝር ከካርቶግራፊ ክፍል ካለው ካርታና መግለጫ ካላቸው የቆጠራ ቦታዎች ዝርዝር ጋር እንዲገናዘብና ልዩነቶች እንዲለቀሙ የማድረግ ሥራ ተካሄዷል።

- ለወረዳ ኔት ፕሮግራም የተሰበሰቡ ፎርማቶች ፅንሰ ሃሣቦችና ፍችዎቻቸውን በየዘርፉ በመተንተን ትርጉማቸው በግልጽ የተቀመጡትንና ያልተቀመጡትን የመለየት ሥራ ተከናውኗል።

- አጠቃላይ በስታንዳርድ ደረጃ ሊያገለግሉ የሚችሉ ጽንሰ ሃሳብና ፍችዎቻቸው የማዘጋጀቱ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

- በ1998 ዓ.ም ለሚካሄደው የግብርና ናሙና ጥናት አዲስ ለተመረጡና ካርታቸው ለጠፋ የቆጠራ ቦታዎች ካርታ ተዘጋጅቷል፡፡

- በተለያዩ ክልሎች ሥር ለሚገኙ የቆጠራ ቦታ በክፍለ ከተማ፣ በከተማና በቀበሌ ደረጃ ተለይተው ለአሠራር ምቹ በሆነ ሁኔታ ተጠርዘው እንዲቀመጡ ተደርገዋል፡፡

- በስምንት ዞኖች ለህዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ የሚያገለግሉ ባለ 1:50,000 መስፈርት የቶፖግራፊ ካርታዎችን በመለየት ተገዝተው ለሚመለከታቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ተሠራጭተዋል፡፡ እንዲሁም 46 የወረዳ ካርታዎች ለውጭ ተገልጋዮች ተሸጠዋል፡፡

## 6. መረጃ ማቀነባበርን በተመለከተ

### 6.1 የኤዲቲንግና ኮዲንግና ዳታ ኢንትሪ

በዕቅድ ዘመኑ የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ውስጥ የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀላቸው የ1996 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ የ1997 የበልግ ጥናት፣ የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ የ1998 ወርሃዊ የዋጋዎች ጥናት፣የ1998 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ ዳታ ኢንትሪና የክሊኒንግ ሥራ ተከናውኗል፡፡ 1997 የሰው ሃይል ጥናት፣ የ1998 የሰብል ትንበያ ጥናት፣ የሠፈራ ጣቢያዎች ሰብል ትንበያ ጥናት፣ የ1998 የዋጋዎች ጥናት የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ተጠናቆ የዳታ ኢንትሪና ክሊኒንግ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

### 6.2 የሠንጠረዥ ዝግጅት

- የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባራት የተከናወነላቸው ወርሃዊ የዋጋ ጥናቶች የኢንዴክስ መረጃ፣ የ1997 የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ የ1996 የበልግ ጥናት የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን የ1997 በመሬት አጠቃቀም የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት፣ እንዲሁም የ1998 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ጥናት ሠንጠረዦች ተዘጋጅተዋል፡፡

- በሌላ በኩል መረጃዎችን ወደ SPSS Format በመለወጥ ለተጠቃሚዎች በሚያመች መንገድ ለማዘጋጀት በታቀደው መሠረት የ1996 የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የ1997 አጠቃላይ የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት፣ የ1997 የታረሰ መሬትና የምርት መጠን ጥናት፣ የ1997 የመሬት አጠቃቀም፣ የ1997 የሸማቾች ዋጋ ጥናት፣ የ1997 የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣ የ1997 የሆቴሎች ዋጋ ጥናትና የቤት እንስሳት የጥናት መረጃዎችን ወደ SPSS Format የመለወጥ ሥራ ተከናውኗል።

## 6.3 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- በመ/ቤቶችና በድርጅትና በግለሰብ ደረጃ ለቀረቡ የመረጃ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል።

- እ.ኤ.አ የ2000 Demography and Health Survey (DHS) መረጃ አመልካች በ EthioInfo Database ሥራ ተጠናቋል። የ1996 እና የ1997 የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ጥናት መረጃ አመልካች፣ የ1996 እና 1997 የህዝብ ብዛትና አሠፋፈር ሁኔታ አመልካች በ EthioInfo Database የማዘጋጀቱ ሥራ ተጠናቋል።

# 7. ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን በተመለከተ

- በዕቅድ ዘመኑ ሩብ ዓመት ለICT አቅም ግንባታ ከUNDP ተገዝተው የመጡ ዕቃዎችን አስፈላጊውን የኮንፊገሬሽን ሥራ በመሥራት ዕቃዎችን በመረከብ ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል።

- የመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ተጠናቆና ተመርቆ ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ በዚሁ ድረ-ገጽ መ/ቤቱ ውስጥ /HOST በማድረግ/ በየትኛውም ዓለም ያለ ተጠቃሚ እንዲያገኘው የሚያስችለውን የDomain Registration እና Public IP ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን በመግዛት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። በመ/ቤቱ ኔትወርክ የተገናኘላቸው የሚመለከታቸው የመ/ቤቱ ባለሙያዎችም Official e-mail አካውንት እንዲያገኙ ተደርጓል።

- በማዕከላዊ የመረጃ ማዕከል ተከማችተው ከነበሩ ጥናቶች ውስጥ፣ የ1996፣ 1998፣ 2002፣ 2004፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ደህንነት ጥናቶች፣ የሁለት ዓመት የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናቶች፣ በማህበራዊ ስታቲስቲክስ

መምሪያ የተጠኑ የተለያዩ ጥናቶች፣ በኢንድስትሪ መምሪያ የተወሰኑ ጥናቶች እንዲሁም የ2004 የግብርና ጥናት የመሬት ስፋትና ምርት መጠንን የሚመለከት Dissemination Toolkit በመጠቀም ለተጠቃሚዎች አመች በሆነ የማሠራጫ መንገድ ተደራጅተው እንዲቀመጡ ለማድረግ የData Archive ሲስተማቸው በአብዛኛው ተጠናቋል።

- የመ/ቤቱን የሰው ኃይል መረጃ አያያዝ ሥርዓት ዘመናዊ አሠራርን የተከተለ እንዲሆን ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ሥራ በማከናወን ለፐርሰኔል ክፍል ሙያዊ ዕገዛ ተደርጓል።

- ብዛት ያላቸውን ኮምፒውተሮች መለዋወጫን የመቀየር ሥራ፣ የኮንፊገሬሽን ሥራ እንዲሁም የኮምፒውተር ጥገናና Memories የመጨመር ተግባራት ተከናውነዋል።

- የServer ክፍሉ ደረጃውን የጠበቀ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ዕቃዎችን ዝርዝር በማቅረብ ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር የዕቃ መረጣ ተካሄዶ ግዥውን ለመፈጸም ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተዋል።

## 8. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት

- በ1997 የዕቅድ ዘመን በመ/ቤቱ ይካሄድ የነበረው የአሠራርና የአገልግሎት አሠጣጥ ጥናት (BPR) የግብርና ስታቲስቲክስ የመረጃ አቅርቦት የማሻሻያ ጥናትን በሚመለከት የመጀመሪያው ምዕራፍ ተጠናቆ ማሻሻያው የሚተገበርበት መርሃ ግብር በረቂቅ ደረጃ ሲጠናቀቅ፣ የመረጃ ክምችትንና ስርጭትን በሚመለከት የመጨረሻው የማሻሻያ ጥናት ተጠናቆ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚመራው የበላይ አስተባባሪ ገምጋሚ ኮሚቴ ጋር ውይይት ለማድረግ ፕሮግራም ተይዟል።

- በተመሳሳይ ሁኔታ በመ/ቤቱ በሌሎች የሥራ ክፍሎችም ሲካሄድ የነበረው የአሠራርና የአገልግሎት አሠጣጥ ማሻሻያ ጥናትን በሚመለከት መ/ቤቱ የአደረጃጀት ማሻሻያ እየተካሄደ በመሆኑ ሁሉም የሥራ ክፍሎች የየሥራ ክፍላቸውንና የሥራ መደቦችን በመሥራት ላይ በመሆናቸው ይህ የተያዘው ሥራ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የማሻሻያ ጥናቱ ለጊዜው እንዲዘገይ ተደርጓል።

- መ/ቤቱ ለመንግሥት ያቀረበው አዲስ አደረጃጀት የተደገፈለት በመሆኑ የመምሪያዎች፣ የቡድኖች፣ የአገልግሎቶችና የዋና ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት፣ የሥራ ክፍሎች የሰው ሃይል ፍላጐት ተዘጋጅቶ ለፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቀርቧል።

## 9. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አልግሎት

- በ1998 የዕቅድ ዘመን የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ውስጥ በመ/ቤቱ የተዘጋጁ 2,800 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶች ለመንግሥት፣ ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ለምርምር ማዕከላት በነፃ ተሠራጭተዋል። እንዲሁም 743 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶችና የስታቲስቲክስ መጽሔቶች በብር 17,603.30 ሽያጭ የተፈፀመ ሲሆን ብር 2,180 የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል በጠቅላላው ከሽያጭና ከአገልግሎት ክፍያ ብር 19,783.30 ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል።

- የመ/ቤቱ ልሳን የሆነው ልሳነ ማስባ ቅጽ 4 ቁጥር 5 መጽሔት 2,000 ኮፒ ታትሞ ተሠራጭቷል።

- የመ/ቤቱን የ1997 የዕቅድ አፈጻጸም የመ/ቤቱን የ5 ዓመት የትኩረት አቅጣጫና ድረገጽ ግንባታ፣ በመ/ቤቱ የተካሄደውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት በተመለከተ ጉዳዩ በሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል። እንዲሁም ሌሎች በመ/ቤቱ የተከናወኑ ተግባራት በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጦች ሽፋን እንዲያገኙ በማድረግ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ተሞክሯል።

- የመ/ቤቱ ቤተ መጻሕፍት ለመሥሪያ ቤቱ ሠራተኛና ከውጭ ለሚመጡ ተገልጋዮችና ተጠቃሚዎች ያልተቋረጠ የንባብ፣ የመረጃ አቅርቦትና የትውስት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

- በ1998 የዕቅድ ዘመን በመጀሪያው ሩብ ዓመት ውስጥ 75 የመ/ቤቱን ሪፖርቶች በመረከብና 24 ልዩ ልዩ አዳዲስ የውጭና የአገር ውስጥ ህትመቶችን በልውውጥና በስጦታ በማሰባሰብ ቤተ መጻህፍቱን ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል።

- በሌላ በኩል በቤተ መጻህፍቱ ውስጥ ለውጭ ተገልጋዮች የፎቶ ኮፒ አገልግሎት በመስጠት ብር 477 ለመንግሥት ገቢ ሊሆን ችሏል፡፡

- የ1998 አዲስ አመትን ምክንያት በማድረግ የመልካም ምኞት መግለጫ የቀን መቁጠሪያ ዝግጅቱ ተጠናቆ በመታተም ላይ ይገኛል፡፡

## 10. የኦዲት አገልግሎት

- በ1998 የዕቅድ ዘመን በዚህ ሩብ ዓመት ውስጥ የመ/ቤቱን ገንዘብ ቤትና የዕቃ ግምጃ ቤት ሐምሌ 1/1997 ዓ.ም በማሸግ የገንዘብ ቤቱ የምርምራ ሥራና እንዲሁም የዕቃ ግምጃ ቤቱ የአላቂ ንብረቶች ቆጠራ ተደርጉና ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተላልፏል፡፡

- የመ/ቤቱ የየወሩ የሳጥን ወይም የካዝና ምርመራ ተካሂዶ ሪፖርቱ ለመ/ቤቱ የበላይ አካል የቀረበ ሲሆን፣ የዕቃ ግምጃ ቤት የቋሚ ንብረት ገቢና ወጪ ምርመራም ተካሂዷል፡፡ እንዲሁም የመ/ቤቱ የመኪና መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ቆጠራው ተካሂዶ በምርመራ ላይ ይገኛል፡፡

- ከሐምሌ ወር 1996 ዓ.ም እስከ ግንቦት 1997 ዓ.ም ያለው የ1997 ዓ.ም የገቢና ወጪ ሂሣብ ምርመራ ተደርጓል፡፡

## 11. ሕግ አገልግሎት

- ከሰኔ 30/1997 በፊት መ/ቤቱ የጉዳት ካሳ እንዲከፍላቸው በተለያዩ ፍ/ቤቶች ሁለት ግለሰቦች በጠቅላላው በብር 74,080.20 እንዲሁም ሁለት የመ/ቤቱ ሠራተኞች ያላግባብ በዲስፕሊን ክስ ደመወዛችን ስለተቆረጠብን ይመለስልን በማለት ባቀረቡት ክስ ላይ በዚህ ሩብ ዓመት ክትትል የተደረገ ሲሆን ጉዳዩ በቀጠሮ ላይ ይገኛል፡፡

- በሌላ በኩል ሁለት የመ/ቤቱ ሠራተኞች በነበሩበት ወቅት ያጉደሉትን ብር 94,307.33 የመንግሥት ገንዘብ እንዲከፍሉና አንድ ግለሰብ ደግሞ መ/ቤቱ ካስተማረው በኋላ የተማረበትን ወጪ መ/ቤቱን ሳያገለግል በመልቀቁ የትምህርት ወጪውን ብር 47,593.92 እንዲከፍል በተለያዩ ፍ/ቤቶች መ/ቤቱ ክስ መስርቶባቸው ጉዳዩ በቀጠሮ ላይ ያለ ሲሆን ክትትል እየተደረገበት ይገኛል፡፡

- ኒያላ ኢንሹራንስ በመ/ቤቱ ባቀረበው ክስ ላይ በዚሁ ሩብ ዓመት የተደረገው ክትትል መድን ድርጅት ክስ ከቀረበበት ውስጥ ብር 8,231.20 እንዲከፍል ፍ/ቤቱ በመወሰን መ/ቤቱን በነፃ አሰናብቶታል።

## 12. ፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት

- በ1998 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ከመንግሥት የተፈቀደዉን ካፒታል በጀት ከሚመለከታቸዉ መምሪያዎችና አገልግሎቶች ጋር በመሆን በወርሃዊ የሥራ መርሃ-ግብሩ መሠረት ወርሃዊ የገንዘብ ፍላጎት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላለፍ ተደርጓል።

- የ1998 በጀት ዓመት የስታቲስቲክስ የሥራ ዕቅድን በተፈቀደው በጀት መጠን አስተካክሎ ለመ/ቤቱ የበላይ አካልና ለሁሉም መምሪያዎችና አገልግሎቶች ለክትትል እንዲያመች አዘጋጅቷል።

## 13. የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት

### 13.1 የሰው ኃይል

በ1998 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,538 ቋሚና 2,339 የኮንትራት በጠቅላላው 3,877 ሠራተኞች ነበሩ። በዚህ ሩብ ዓመት ውስጥ ከቋሚ ሠራተኞች መካከል 10 በራሳቸው ፈቃድ የለቀቁ ሲሆን፣ 3 በዲስፕሊን ጉድለት ከሥራ ተሰናብተዋል። እንዲሁም 1 በጡረታ የተገለሉ ሲሆን፣ 7 በሞት ተለይተዋል። በአንጻሩም የ18 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር ሲፈጸም 1 በዝውውር እንዲሁም 1 ደግሞ በመንግሥት ትዕዛዝ ወደ መ/ቤቱ እንዲመለሱ ተደርጓል። በሌላ በኩል ከ2,339 የኮንትራት ሠራተኞች ውስጥ በዚህ ሩብ ዓመት 2,038 ከመ/ቤቱ ሲሰናበቱ 22 ሹፌሮች፣ 10 የሂሳብ ሠራተኞች 2፣ ኦዲተሮች፣ 106 ጀማሪ መረጃ ሰብሳቢ፣ 31 ዳታ ኢንትሪ ኦፕሬተሮች፣ 13 የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪዎችና 1 የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ ቅጥር ተፈፅሟል።

በዚሁም መሠረት በ1998 የዕቅድ ዘመን በጀመሪያው ሩብ ዓመት መጨረሻ ላይ ያለው በቅላላ የሰው ኃይል 2,023 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1,537 ቋሚና 486 የኮንትራት ሠራተኞች ናቸው።

ሠንጠረዥ 2 <u>የሰዉ ኃይል ሁኔታ</u>

| ተ.ቁ | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,538 | 2,339 | 3,877 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 18 | 185 | 203 |
| 3 | በመንግሥት ትዕዛዝ ወደ ሥራ የተመለሱ | 1 | - | 1 |
| 4 | በዝውውር ወደመ/ቤቱ የመጡ | 1 | - | 1 |
| 5 | ሥራ የለቀቁ | (13) | (2,038) | (2,051) |
| 6 | በጡረታ የተገለሉ | (1) | - | (1) |
| 7 | በሞት የተለዩ | (7) | - | (7) |
| 8 | አሁን በሥራ ላይ ያሉ | 1,537 | 486 | 2,023 |

ከዚህ በታች በሠንጠረዥ የተገለፀው የሰው ኃይል በአገልግሎት ዓይነት ሲተነተን ቋሚ ሠራተኞችን በሚመለከት 148 በፕሮፌሽናል 816 መለስተኛ ፕሮፌሽናል፣ ሲሆን 573 የአስተዳደርና የጽፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው::

በ1998 የዕቅድ ዘመን በመጀመሪያው ሩብ ዓመት መጨረሻ ላይ ያሉት የመ/ቤቱ ቋሚና የኮንትራት ሠራተኞችን ሁኔታ በሥራ መደብ በመለየት በሚከተሰው ሠንጠረዥ ለማቅረብ ተሞክሯል::

<u>የሠራተኞች ሁኔታ በሥራ መደብ</u>

ሠንጠረዥ 3

| ፆታ | ቋሚ | | | | ኮንትራት | | | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፕሮፌ ሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | ፕሮፌ ሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | |
| ወንድ | 128 | 722 | 342 | 1,192 | 47 | 145 | 128 | 320 | 1,512 |
| ሴት | 20 | 94 | 231 | 345 | 2 | 28 | 136 | 166 | 511 |
| ድምር | 148 | 816 | 573 | 1,537 | 49 | 173 | 264 | 486 | 2,023 |

## 13.2 የበጀት አጠቃቀም

ለ1998 በጀት ዓመት ለባለሥልጣኑ መ/ቤት ከመንግሥት የተፈቀደለት የመደበኛና የካፒታል በጀት በጠቅላላው ብር 93,132,900 ነው። ከዚህ ውስጥ ብር 36,636,700 ለብሔራዊ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ብር 41,870,000 ለህዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት ለካርታ ሥራ የቅድመ ዝግጅት የሚውል ሲሆን ብር 14,626,200 ለመደበኛ ሥራ ማስኬጃና ለደመወዝ ክፍያ የሚውል ነው።

### 13.2.1 የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

በዕቅድ ዘመኑ ከተመደበው ብር 14,626,200 ውስጥ በዚህ ሩብ ዓመት ውስጥ ማለትም ከሐምሌ 1/1997 ዓ.ም እስከ መስከረም 30/1998 ዓ.ም ድረስ ብር 3,387,350 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ ሆኖ ብር 3,210,593 ሥራ ላይ ውሏል። ሥራ ላይ ከዋለው ብር ውስጥ 3,058,249 (21%) ያህሉ ለደመወዝ የተከፈለ ሲሆን፣ ብር 152,345 (1%) ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የዋለ ነው። በጠቅላላ በዚህ ሩብ ዓመት ሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ ለመ/ቤቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 22% ከመቶው ያህሉን እንደሆነ የሚያመለክት ሲሆን ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ ከሆነው ጋር ሲነፃፀር ደግሞ 95% ያህሉን ነው።

<u>የመደበኛ በጀት አጠቃቀም</u>

ሠንጠረዥ 4

| የወጪ ርዕስ | ለዓመቱ የተመደበ በጀት | በበጀት ዓመቱ ከተፈቀደዉ ዉስጥ ተጠይቆ የመጣ | ተጠይቆ ገቢ ከሆነዉ ዉስጥ ሥራ ላይ የዋለ | የአፈፃፀም በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በሩብ ዓመት | በዓመቱ |
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 |
| ደመወዝ | 13,224,500 | 3,098,682 | 3,058,249 | 99 | 23 |
| ሥራ ማስኬጃ | 1,401,700 | 288,668 | 152,345 | 53 | 11 |
| ድምር | 14,626,200 | 3,387,350 | 3,210,593 | 95 | 22 |

### 13.2.2 <u>የካፒታል በጀት አጠቃቀም</u>

በ1998 በጀት ዓመት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮጀክቶች በጠቅላላው ብር 78,506,700 ተፈቅዶለታል። ከዚህ ውስጥ ብር 36,636,700 ለብሔራዊ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያና ብር 41,870,000 ደግሞ በ1999 ዓ.ም ለሚካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ለካርታ ሥራ የሚውል ነው።

በዚሁም መሰረት የሁለቱን ፕሮጀክቶች የበጀት አጠቃቀም በተናጠል እንደሚከተለው ለማመልከት ተሞክሯል።

ሀ. ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም

በ1998 በጀት ዓመት ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የተፈቀደው ብር 36,636,700 ሲሆን በዚህ ሩብ ዓመት ውስጥ ብር 8,567,658 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ ሆኖ ብር 7,672,459 ሥራ ላይ ውሏል። ሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ ተጠይቆ በእጅ ከገባውና ለመ/ቤቱ ከተመደበው ጋር ሲነፃፀር አፈፃፀሙ በቅደም ተከተል 89% ፣ እና 21% እንደሆነ ያመለክታል።

•

የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም በጀት አጠቃቀም

ሠንጠረዥ 5

| የሂሣብ መደብ | ለ1998 በጀት ዓመት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ከገ/ኢ/ል ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የሆነ | ገቢ ከሆነው ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው | አፈጻጸም በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ከሩብ ዓመቱ | ከዓመቱ |
| 6113 | 13,332,200 | 1,950,700 | 1,582,308 | 81 | 12 |
| 6114 | 3,340,200 | 518,700 | 367,741 | 71 | 11 |
| 6123 | 880,900 | 49,260 | 123,030 | 249 | 6 |
| 6211 | 366,200 | - | - | - | - |
| 6212 | 300,000 | 55,000 | 66,979 | 122 | 22 |
| 6213 | 350,000 | - | 483 | - | 0.14 |
| 6217 | 3,254,000 | 588,900 | 518,573 | 88 | 16 |
| 6231 | 8,700,000 | 3,320,748 | 3,330,369 | 100 | 38 |
| 6232 | 539,400 | 383,450 | 232,285 | 61 | 43 |
| 6241 | 3,221,000 | 645,400 | 459,590 | 71 | 14 |
| 6243 | 60,000 | 12,000 | - | - | - |
| 6252 | 642,700 | 359,300 | 320,748 | 89 | 50 |
| 6254 | 1,090,100 | 577,500 | 580,367 | 100 | 53 |
| 6257 | 40,000 | 10,400 | 10,210 | 98 | 26 |
| 6258 | 340,000 | 72,100 | 39,400 | 55 | 11 |
| 6259 | 55,000 | 14,200 | 19,982 | 141 | 36 |
| 6271 | 125,000 | 10,000 | 20,395 | 203 | 16 |
| ድምር | 36,636,700 | 8,567,658 | 7,672,460 | 89 | 21 |

ሰ. <u>ለቆጠራ ካርታ ሥራ ፕሮግራም</u>

በ1999 ለሚካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት ለቆጠራ ቦታ ካርታ ዝግጅት በ1998 በጀት ዓመት ብር 41,870,000 ከመንግሥት የተፈቀደ ሲሆን፣ በዚህ ሩብ ዓመት ብር 13,739,201 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ ሆኖ ብር 13,028,215 ሥራ ላይ ውሏል:: ጥቅም ላይ የዋለው ገንዘብ ተጠይቆ ገቢ ከሆነውና ለዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር በቅደም ተከተል 95 % እና 31% ከመቶው ያህሉን ነው::

<u>የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ፕሮግራም በጀት አጠቃቀም</u>

ሠንጠረዥ 6

| የሂሣብ መደብ | ለ1998 በጀት ዓመት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ከገ/ኢ/ል ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የሆነ | ገቢ ከሆነው ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው | አፈጻጸም በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ከሩብ ዓመቱ | ከዓመቱ |
| 6113 | 5,777,200 | 1,151,700 | 915,841 | 79 | 16 |
| 6114 | 1,850,400 | 224,400 | 194,100 | 86 | 10 |
| 6123 | 315,000 | 31,200 | - | - | - |
| 6212 | 4,300,000 | 30,800 | 22,880 | 74 | 0.53 |
| 6213 | 100,000 | - | - | - | - |
| 6217 | 3,400,000 | 369,800 | 295,300 | 80 | 9 |
| 6231 | 9,500,000 | 1,448,900 | 1,457,269 | 100 | 15 |
| 6232 | 200,000 | 43,700 | 36,066 | 93 | 18 |
| 6241 | 2,100,000 | 348,600 | 63,674 | 18 | 3 |
| 6243 | 180,000 | 34,300 | 9,400 | 27 | 5 |
| 6254 | 177,400 | - | - | - | - |
| 6258 | 130,000 | 28,900 | 16,000 | 55 | 12 |
| 6259 | 90,000 | 18,000 | 8,784 | 49 | 10 |
| 6311 | 13,750,000 | 10,008,901 | 10,008,901 | 100 | 73 |
| ድምር | 41,870,000 | 13,739,201 | 13,028,215 | 95 | 31 |

## 13.3 አገልግሎት ነክ የሆኑ ሥራዎች

### 13.3.1 ጠቅላላ አገልግሎት ዋና ክፍል

- በ1998 በጀት ዓመት በዋናው መ/ቤትና በስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች የደንብ ልብስ የሚያስፈልጋቸውን የሠራተኛ ቁጥር በማጣራት የስም ዝርዝራቸው እንዲሰበሰብ የተደረገ ሲሆን፣ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ውጤትም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲልኩ በተጠየቁት መሠረት ከብዛኞቹ ቅ/ጽ/ቤቶች ምላሽ ተገኝቷል።

- በዕርዳታ የተላኩ 16 ፕሪንተሮች፣ 25 ኮምፒውተሮችና 26 የፎቶ ኮፒ ማሽኖች ገቢ ተደረገዋል። የዋናው መ/ቤት የንብረት ቆጠራ ተደርጎ ሪፖርቱ ቀርቧል።

- የአንድ ዓመት የኮምፒውተር ፕሪንተር የጥገና ኮንትራት በግልጽ ጨረታ በጋዜጣ እንዲወጣ ተደርጎ የአሸናፊውን የመለየት ሥራ በጨረታ ኮሚቴ እየተሠራ ይገኛል።

- የመ/ቤቱን የጽ/መሳሪያ፣ የደንብ ልብስ፣ የህትመት አላቂ ዕቃዎች፣ ቋሚ ዕቃዎችና የካርቶግራፊ ዕቃዎችን ግዥ ለመፈጸም በግልጽ ጨረታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በማውጣት የጨረታ ሰነዱ በመሸጥ ላይ ይገኛል።

- መ/ቤቱ የተጠቀመባቸውን የስልክ፣ የመብራት፣ የውሃ ፍጆታና የኢንተርኔት ክፍያዎችን በሚመለከት አስፈላጊውን መረጃ ቢሉን በማየት ክፍያው እንዲፈጸም ተደርጓል።

- በመ/ቤቱ የሚገኙትን የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች መ/ቤቱ ሊጠቀምባቸው የሚችሉትንና የማይጠቀምባቸውን በመለየት በንብረት አወጋገድ መመሪያ መሠረት እንዲከናወን ለማድረግ ለሚመለከተው አካል በማሳሰቢያ ተጠይቋል።

- በመ/ቤቱ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት በሰጡና በአሁኑ ሰዓት ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ልዩ ልዩ የመረጃ ወረቀቶች በንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ አማካኝነት በተወሰነው መሠረት እንዲሸጥ ተደርጓል።

### 13.3.2 ትራንስፖርትና ጥገና ክፍል

- በዚህ ሩብ ዓመት ውስጥ በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሚገኙ የ105 ተሽከርካሪዎችን የኢንስፔክሽን ሥራ በማካሄድ በተለያዩ የውጭ ጋራዦች በማስገባት የጥገና ሥራቸው በመከናወን ላይ ያለ ሲሆን በባለሙያዎች ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡
- የመ/ቤቱ 17 ተሽከርካሪዎችም በዋናው መ/ቤት ጋራዥ የጥገና ሥራ የተካሄደ ሲሆን ዓመታዊ የተሽከርሪዎች ምርመራ ዝግጅትም ተጠናቋል፡፡
- በጨረታ ኮሚቴ የተመረጡ የ6 ጋራዦች ውል ተፈጽሟል፡፡ እንዲሁም የ248 ተሽከርካሪዎች የኢንሹራንስ አገልግሎት እንዲያገኙ ከመድን ጋር የውል ዕድሳት ተፈጽሟል፡፡
- 10 ተሽከርካሪዎች በመድን ድርጅት ጥገናና ዕድሳት ተደርጎላቸው ለስምሪት ብቁ ሆነዋል፡፡
- በዋናው መ/ቤት ለሚገኙ ተሽከርካሪዎች 5,418 ሊትር ቤንዚን፣ 3,452 ሊትር ናፍታ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ አጥበት ግሪስና ዘይት እንደ አስፈላጊነቱ ተሽከርካሪዎች እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- ለ25 ቱም የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀምን በሚመለከት መመሪያ ተዘጋጅቶ ተሠራጭቷል፣ የተሽከርካሪ የጥገና ሂደታቸውም ምርመራ መካሄዱ ተረጋግጧል፡፡

### 13.3.3 ሕትመት ዋና ክፍል

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ድረስ በጠቅላላው 23,418 ጥራዝ ባለ 5,145,621 ገጾች የተለያዩ የሕትመት ሥራዎች ለመ/ቤቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች አገልግሎት ሰጥቷል፡፡

## 14. በዕቅድ አፈፃፀሙ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

እያደገ የመጣውን የመረጃ ፍላጐት ለማሟላት እንዲቻል በየወቅቱ ቁጥራቸው በዛ ያለ ባለሙያዎች የሚቀጠሩ ሲሆን፣ ከዚህ በፊትም የተቀጠሩት ለሥራቸው ምቹ የሆነ ቢሮ ለማግኘት ከመ/ቤቱ አቅም በላይ እየሆነ መጥቷል። በተለይም ደግሞ የሕዝብና ቆጠራ ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 449/97 መሠረት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲን የኮሚሽኑ ጽ/ቤት እንዲሆን የደነገገ ሲሆን፣ በጽ/ቤቱ የሚሠሩ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ተረክቦ በማሰራት ላይ ነው። ሆኖም በአንድ አካባቢ አድርጐ ለማሠራት በቂ የሥራ ቦታ ባለመገኘቱ በሁለት ቦታዎች ሆነው ሥራቸውን እንዲሰሩ እየተደረገ ይገኛል። ይህ ደግሞ በአጠቃላይ የኤጀንሲው ሥራ ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል።

ይህም በመሆኑ በርካታ የሥራ ኃላፊዎችና ኤክስፐርቶቻቸው ተራርቀው የሚሰሩበት እንዲሁም አንድ ክፍል ከአቅም በላይ የሆነ የሰው ብዛት እንዲይዝ በማድረጋችን ቢሮዎቻችን ለሠራተኞች የተመቹ የሥራ ቦታ ሊሆኑ ባለመቻላቸው የሠራተኞች የሥራ ተነሣሽነት እየቀነሰ የሚመጣበት ሁኔታን እየፈጠረ ይገኛል። በተጨማሪም ከፍተኛ የመንግስት ሃብት የወጣባቸው የተለያዩ የመስክ መገልገያ ዕቃዎች፣ በተለያዩ ጊዜያት መረጃ የተሰበሰበባቸው የጥናት ዶኩመንቶችና ሌሎች ቁሣቁሶች አመች የሆነ ማከማቻ መጋዘን ባለማግኘታቸው ችግሩን የተደራረበ አድርጐታል። እንዲሁም በመላው አገሪቱ የተከፈቱ የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ላይ ተመሣሣይ የሆነ የቢሮና የመጋዘን ችግር ያላባቸው ሲሆን፣ በዓመት መንግሥት ለዋና መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶቹ ከግማሽ ሚሊዩን ብር በላይ ለኪራይ ወጪ ያደርጋል በመሆኑም ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶቻችን ለሥራ አመቺ የሆነ ቢሮ ለማግኘት እንድንችል ህንጻዎቹ የሚገነቡበት መንገድ በማጥናት ላይ ስለሆንን ጥናቱን በተግባር ለመተርጎም ከመንግስት የበጀት ድጋፍ አስፈላጊ ይሆናል።